# የሱዳን መገንጠል ለምን ተፈለገ? በማን ተፈለገ?

ከ - ካሳሁን

ፖለቲካ በግልብና በጥራዝ ነጠቅነት የሚፈነጭበት መስክ አይደለም። የሀገርን መፃኢ ዕጣ የሚመለከት ነውና በተለይም ተጨባጩን ሁኔታ በሚገባና በትክክል ተንትኖ ዕቅድና ስልትን ለመቀየስ ስንነሳ ሁኔታዎችን በሚገባ መመርመርና ላለመሳሳት መጣር ይኖርብናል። በሰሞኑ ቱኒዝያና ደቡብ ሱዳንን በተመለከተ አወቅን ባዮች ሲፅፉ የሚነበበውና ሲለፍፉ የሚደመጠው አሳሳቢ በመሆኑ ለመሆኑ ቢያንስ የደቡብ ሱዳንን መገንጠል ማን ፈለገ? ለምንስ ተፈለገ በሚለው ላይ መተቸቱ አስፈላጊ ሆኗል። በተለይም ከፖለቲካ መቃብራቸው ድንገት ወጥተው፣ ከተጣሉበት የፖለቲካ ምድረበዳ አመለጥን ብለው የሱዳንን መገንጣጠል እንደግፋለን የሚሉ ጩኸቶች መድረክ ስላጣበቡ አላዋቂነት በጫጫታ ብዛት ብልህነት እንዳይመስል ከወዲሁ መጋለጡ ተገቢ ነው።

ተገቢውን ትንተና አድርገን ትክክለኛ አቋም ለመያዝ ስንጥር ሳያልሙ ምላጭ መሳብ እንዳይሆን በቅድሚያ የሁኔታውን ወይም ጥያቄውን ታሪክና አነሳስ በመረጃ ተደግፈን መመርመር መቻል አለብን። አዲስ ወጥ ሰሪ ዝንጅብል ታበዛለች እንዲሉ ወደ ፖለቲካው ድንገት ዘው ያሉት ትንተና ብለው ነጩን ከጥቁሩ አዋህደውና አደናግረው ያቀርባሉ። በየሀገሩ ያሉ ሁኔታዎች የተመሳሰሉ ቢመስሉም ልዩ መሆናቸውን ይክዳሉ። አዳዲስ የፈጠራ ታሪክንም ሀቅ ብለው ያናፍሳሉ። ለዚያም የጥያቄውን ሁለንተናዊ ይዘት ማጤን ያስፈልጋል። በጉዳዩ የገቡና ሊገቡ የተነሱትም ሀይሎች ማንነታቸውና ዓላማቸው ግባቸው መታወቅ ይኖርበታል። ማን ተጠቃሚ ማን ተጎጂ የሚለውም መጠናት አለበት። የሀገር ጉዳይ እስከሆነም የአካቢና ዓለም አቀፍ ሁኔታም የምርምሩ አካል ሆኖ መገኘት ይኖርበታል። ግራ ቀኙንም ጠላት ብሎ ማጥቃቱ ስልትና ብልሀነት ሳይሆን የፖለቲካ ጨቅላነት ነው። ለምሳሌ በደፈናው የደቡብ ሱዳን ሕዝብ ተበድሏልና ይገንጠል ብሎ መጮህ ያስገምታል እንጂ አያሳምንም። በኤርትራ የነበረው ሕዝብ መበደሉና መጠቃቱም የታወቀ ቢሆንም ሕዝብ ተበደለ በሚል ሀገር ይገነጣጠል ብሎ ሰበካ ከጎጂነትም በላይ ቅጥ ትና ሀላፊነት የጎደለው ነው የሚሉ ዛሬ ገልበጥ ብለው ደቡብ ሱዳን ተበድሏልና ይገንጠል ሲሉ ለትዝብት ይዳረጋቸዋል። ለዚህም ነው የመገንጠልን ምርጫ ጎጂ ነው ብለው ብዙዎች ሲቃወሙ የቆዩት። እዚህ ላይ ማንሳት የምንገደደው ሌላ ሀቅ ደግሞ የፈረደበትን ዋለልኝ መኮንንን ሰይጣናዊ ተልዕኮ በመስጠት የግንጠላ ዋና አቀንቃኝ አድርገው በማቅረብ ያን የታገለ ትውልድ ሁሉ ፀረ ኢትዮጵያ ብለው ሊያወግዙ የሚዳክሩ አድህሪዎች መኖራቸውን ነው (በቀጣይ ፅሁፍ በነዚህላይ እናተኩራለን) ። በዓለም ደረጃም ብዙ ሕዝቦች ይበደላሉ--ስለዚህ ግን ሀገሮች ይፈራርሱ ብሎ መደምደም አይቻልም። ሶቭየት ሕብረትንና ዩጎዝላቪያን ያፈረሱት ሀይሎች ለሕዝቦቹ አዝነው ሳይሆን ሁለቱን ሀገሮች ማፍረስ ለበላይነታቸው አስፈላጊና ጠቃሚ ስለሆነ ነው። ይህን የፖለቲካ ሀ ሁ ያላወቁ ሰዎች በመድረክ ለመጮህና የሰከነ ውይይትን ለማገድ - ለመበጥበጥ ሊፈቀድላቸው አይገባም። የደቡድ ሱዳንን ጉዳይ ልንመረምር ስንነሳ ከደቡብ ሱዳን ባሻገር የመላ ሱዳንና የአከባቢው ሁኔታ አልፎም የአፍሪካን ሁኔታና ጥያቄ ሁሉ በማምት በግድ ይገባል። ዛሬ ደቡብ ሱዳን ተገንጥሏል ማለት እንችላለን። ሂደቱን ፀረ አፍሪካዎቹ ምዕራባውያን ሀይሎችና እነ ጂሚ ካርተርም በሞግዚትነት አጠናቀዋል። ሀቁ ሲነገር ግን የሱዳን ችግር ጀመረ እንጂ አላበቃም። ሀቁ ሲነገር ግን የአካባቢው ቀውስ ሊባባስ ተዘጋጀ እንጂ አልበረደም። ለምን ይህን እንዳልን ከዚህ በመቀጠል ለማስረዳት እንሞክር---

1. <u>የችግሩ መንስዔ</u> ያ ዓለምን ያመሰው የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም። በእስያና በአፍሪካ የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሕዘቦችን ከፋፍሎ፣ አዳዲስ ካርታና ድንበር ቀይሶና ከልሎ ሕዝቦች በቀጣይና የማያባራ ንትርክ እንዲቀየዱ አድርጓል። በዚህም መሰረት የሱዳንን የሰሜንና የደቡብ ሕዝብ በመከፋፈል ዛሬ ለሚታየው ቀውስ መሰረትን ጥሏል። ይህ ቀውስ በሱዳን አምባገነን ገዢዎችም ሲባባስ በችግሩ ለመጠቀም የአፄው አገዛዝና እስራዔልም የደቡብ አማፅያንን በመደገፍ ዘው ቢሉም ችግሩን በዋና ደረጃ ያባባሰው የሱዳን ገዢ ክፍል ነው። የደቡብ ሕዝብን በመጨቆንና በመበደልና ወደ አመፅ በመገፋፋት። ራሱን አንያ ንያ ብሎ የተነሳውን የደቡብ ሽምቅ ተዋጊዎች ቡድን አፄውም እስራዔልም የደገፉት ለየራሳቸው ምክንያት ስለነበራቸው መሆኑ ግልፅ ነው። አፄው ሱዳን የኤርትራ (ጀብሀ) ሽምቅ ተዋጊዎችን ይደግፍ ነበርና ምላሹን እየሰጡት ነበር። እስራዔል ደግሞ ሱዳንን ማዳከም ግብፅን ማዳከም ነው በሚል የሱዳንን መበጣበጥ መፈለጉ አልቀረም። በ1972 አንያ ንያ ና የሱዳኑ ኒሜሪ መንግስት በአዲስ አባባ የሰላም ስምምነት ተፈራረሙ። ሱዳን የኤርትራ ሽምቅ ተዋጊውችን ቢሮዎች ልትዘጋና ድጋፍ ልታግዳቸውም ተስማማች (በስራ አላዋላችውም)። ደቡቦችንም በፖለቲካውና ኢኮኖሚው መስክ ለማሳተፍና መብቶችን ለመጠበቅም ተስማምታ ነበር። ይህ ሁሉ አልሆነም። በ1984 እንደገና አመፅ በደቡብ ተቀሰቀሰ። በዶክተር ጆን ጋራንግ መሪነትም የሱዳን ሕዝብ ነፃነት እንቅስቃሴና ጦር ተመሰረተ/ እስፒኤልኤ/ኤም)። በአጭሩ ለማጠቃለል የደቡብ ሱዳን ችግር በሱዳን ዴሞክራሲና እኩልነት ካለመስፈኑ ጋር የተያያዘ ሆኖ ይህንን ችግር ለማባባስ ግን የቅርብም የሩቅም የሱዳን ተፃራሪዎች ተጠቅመውበታል።

<u>2. የኃይሎች አሰላለፍ</u>

2.1.በሁለተኛው ዙር የደቡብ ሱዳን አመፅ የኃይሎች አሰላለፍ ከበፊቱ ተመሳሳይነትንም ልዩነትንም አንፀባርቋል። በአፍሪካ ቀንድ በአጠቃላይም የኃያላን መንግሥታት ሰልፍ የተለዋወጠ በመሆኑ ይህም በሱዳን ላይ እንደምታና ጫናውን ጥሏል። ሱዳን በኒሜሪ ዘመን ከሶቭየትደጋፊነት ወደ አፍቅሮ አሜሪካ ስትለወጥ (እንደ ዚያድ ባሬ ሶማሊያ ማለት ነው) ኢትዮጵያ ደግሞከመንግሥቱ ስር ወድቃ ወደ ሶቭየት ወዳጅነት ተሸጋገረች። የጆን ጋራንግ እንቅስቃሴም በመንግሥቱ የሚረዳ ነበርናም ወደ ምስራቆቹ ወይም የሶሻሊስት ካምፕ ይባል ወደነበረው አዘነበለ። በመንግሥቱ አቅራቢነት ጋራንግ በሙጋቤ፣ በካስትሮ፣ በቬየትናም ወዘተ በልዩ ልዩ መልክ ይረዳ ነበር። የደቡብ ሱዳንን ዘይት ቤንዚን ና ማዕድን የተመኙ ኩባንያዎች ደግሞ ( ሉንርሆ፣ ሼቭሮን፣ ቶታልወዘተ) በውስጥ ውስጥ ከጋራንግ ተወዳጁ። እስራዔል በዩጋንዳ በኩል ክትትልዋን ብታረግም በቀጥታ ጋራንግን የመርዳት እርምጃ አልወሰደችም። በመሆኑም በዚህ ወቅት የሱዳንን መሰባበር ፈላጊዎች መንግሥቱ፣ ሙሴቬኒ (ዩጋንዳ) ምዕራባውያን በከፊል ነበሩ ማለት ይቻላል።

2.2. ሱዳን ትረዳቸው የነበረችውን የኢትዮጵያ ተቃዋሚ እንቅስቃሴዎች በመጠቀም የጋራንግን ድርጅት ልታጠቃ ከመጣርዋ በተጨማሪ በዩጋንዳም ላይ የጆሴፍ ኮኒን አማፅያን ረድታለች። እንግልክ እንደ ሱዳን ሚሊሺያ ሀይል በመሆን በወለጋ የጋራንግን ታጣቂዎች ለማጥቃት ያደረገውን ጥረት ወያኔም ሁለት ሶስት ባታሊዮን በመላክ ለተወሰነ ጊዜ ሊረዳ ቢሞክርም ጉዳቱ በመብዛቱ የጋራ ጥረታቸው ከሽፏል። ኢሕአፓ ነፃ ባወጣው ግዛት እያቋረጡ ወደ ጎንደር የሚገዙትን ደቡብ ሱዳናውያን ሳይተናኮል በመተዉ ወያኔ ለሱዳን አጋልጦና ነፍሶ ገዚያ ላይ የደቡብ ሱዳን ዜጎችን ማሰልጠኛ ካምፕ አቋቁሟል ብሎ በመክሰስ በኢሕአፓና በሱዳን መካከል ችግር መፍጠሩ የሚታወስ ነው። ኢሕአፓ የስደተኞቹን ወደ ጎንደር ጉዞ ባያደናቅፍም የጋራንግ ጦር ግን የኢትዮጵያ ስደተኞችን እየያዘ ለደርግ ያስረክብ እንደነበርና ይህን በተመለከተም ከኢሕአፓ በኩል ማስጠንቀቂያ እንደደረሰው ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። ነገር ግን አንድ አውቃለሁ ባይ በቅርቡ እንዳወራው ሳይሆን በዚህ ድርጅትና በጋራንግ ድርጅት መካከል በዚያን ጊዜ ምንም ግንኙነት አልነበረም። ኒሜሪ ተገልብጦ በሱዳን ሁኔታ ከመቀየሩ በፊትም የአሜሪካና የእስራዔል ሰላዮች ረሀብተኞችን በሚረዱ

በግብረ ሰናዮች ሽፋን ወደ ሱዳን በሰፈው ገብተው እነ ወያኔን ሲረዱ በተለይም የቤተ እስራኤሎች
ን ጉዞ (ኦፕሬሽን ሙሴን አዘጋጅተው) ተግባራዊ አድርገዋል። አሪዬል ሻሮን የእስራኤልን በግልቡ
ከታየ ተቃራኒ መሳይን ፖለቲካ በማንፀባረቅ የኒሜሪም ወዳጅ ነኝ ይል ነበርና ሻሮን ኒሜሪ በቤተእ
ስራኤሎች ጉዞ እንዲተባበረው ጠይቆት ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ የፃፉት እንዳጋለጡት በግንቦት 19
82 የሱዳኑ መሪ ኒሜሪና የፀጥታ ሀላፊው ከሻሮን ጋር የሳውዲው ሚሊዮኔር/ቱጃር በተገኘበት በኬን
ያ ተሰብስበው በተደረገው ንግግር ኒሜሪ በክፍያ ተደልሎ እስራኤል የሞሳድ/ፀጥታ/ ሰራተኞችዋን
ሱዳን ልካ ቤተ እስራኤሎችን ከኢትዮጵያ አውጥታ ትወስድ ዘንድ ፈቀደ። በዚሁ ዘመቻ ሙሴ
የኤርትራው ጀብሀ ድርጅትና ወያኔ ክፍያ ወስደው የተባባሩ ሲሆን ከኢሕአፓ ተበትነው ሱዳን ገ
ብተው የነበሩና ዛሬ በአሜሪካ ያሉ ጥቂት ግለሰቦችም በግል ደረጃ ለእስራኤልም ለአሜሪካም ተቀ
ጥረው ይህን ዘመቻ ለማሳካት ሰርተዋል። (ከተነሳንበት ጉዳይ በስተጎን ደግሞ በቤተ እስራኤሎች ጉ
ዞ ፀረ እስራኤል ነን ይሉ የነበሩት ሱዳኖችም ሆኑ ሳውዲዎች ከሞሳድና ሲአይኤ ጋር መተባበራቸ
ውን ያጤኗል)። የሱዳን ትብብር ተጋልጦ ሲቋረጥም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የአሜሪካው የስለላ
ድርጅት ሲ አይ ኤ ንግስተ ሳባ የሚል ስያሜ የያዘ ዘመቻ ከፍቶ 650 ቤተ እስራኤሎችን ከሱዳን

2.3. በጁን 30/1989 በጀኔራል አማር በሺርና በአክራሪው ሀሰን ቱራቢ የተካሄደው መፈንቅለ መ
ንግሥት የሱዳንና የአካባቢውን ሁኔታ ለወጠው። ከአራት ወር በኋላም የበርሊን ግምብ ፈረሰ፡
የሶቭየት ሀበረትም ፍፃሜ ደወል በጎርባቾቭ ራሱ ረጂነት ተደወለ። የሶቭየትን ድጋፍ ያጣው
የደርጉም የቀብር ቀን ነገ መሆኑ ታየ። የቱራቢ እስላም አክራሪ አቅዋም ሱዳንን ወደ ሃማስ፥
ሂዝቦላህ፡ ኦሳማ ቢን ላደንና ኢራቅም ጎን ሲወስዳት (ሱዳን ኢራቅ ኩዌትን ሲወር ደግፋለች) ምዕ
ራባውያንም እንደገና በጠላትነት እንዲፈርጇት አደረገ ። እስራኤልም ከጋራንግ ተጠጋጋች። ይህ
በዚህ እንዳለ በሱዳን ይረዱ የነበሩት ወያኔና ሻዕቢያ ለስልጣን ሲበቁ (የበሺር አማካሪ ፋቲህ ኤርዋ
በወያኔ በገንዘብ የተገዛ ነበር) ወያኔ ለሱዳን ወሮታና ድጋፍ ለመክፈል የደቡብ ሱዳን ድርጅት አባ
ሎችንና በኢትዮጵያ ሰፍረው የነበሩትን አማፅያን ወደ ኬንያ አባረረ ። የኢትዮጵያ መሬትን ተጠቅ
መው የሱዳን ወታድሮች ደቡቦቹን እንዲያጠቁ ተደርጎም ነበር። ሄርማን ኮኸንና አብዱል አባ ቦራ
የተባለውም ወደ ናይሮቢና ካምፓላ ዘልቀው እነ ጋራንግ ከኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሀይሎች ጋር ትብ
ብር ካደረጉ ብዙ ጥቃት ከምዕራቡ እንደሚደርስባቸው አስፈራሩ። በኬንያ ዩኒሴፍ ተቀጠረ ተብሎ
ምንም ሳይሰራ ብዙ ሺ ዶላር ይከፈለው የነበረው አብዱል መሀመድ አባ ቦራም በእንግሊዝና በአሜ
ሪካ የስለላ ድርጅቶች በመረዳትና በገንዘብና ሴቶች በመጠቀም የጋራንግን ድርጅት ሊከፋፍል ቻለ
። ለዚህ የጋራንግ አምባገነናዊነት ደቡብ ሱዳኖች በጎሳ መለያየት የራሱን አስተዋፅዖ ማድረጉ ባይካ

ድም። በዚህም መሰረት የኑዌር ጎሳ አባል የሆነው ሪያክ ማሻርና ሺሉኩ ላም አኮል ሌሎችን ጨምረ
ው ተገነጠሉና የሱዳን ሕዝብ ነፃ አውጪ እንቅስቃሴ (ናስር) የሚል አንጃ መሰረቱ። ሪያክ ማሻርም
ዉሮት እንግሊዛዊ ሴተ አግባ--ሴትየዋም ከተወሰነ ጊዜ በሁዋላ ግልጽ ባልሆነ የመኪና አደጋ
ስትገደል አንዳንድ ታዛቢዎች የእንግሊዝ የስለላ ተቋም ሰራተኛ ነበርች ይላሉ። አንጃውም አፍረሶ
መፈራረስ የአንጃ ጠባይ ነውና ተከፋፍሎ ማሻርም ሌሎችም ወደ በሺር መንግስት ገብተው የቀድ
ሞ ድርጅታቸው ላይ ከባድ ጉዳት አደረሱ። አሜሪካና እንግሊዝ በመሩት የምዕራባውያንም ዘመቻ
ኢሳያስ፡ ሙሴቬኒና መለስ ዜናዊ (በወቅቱ ሶስቱ መሰኪተሮች ወይም በክሊንተን ወጣት ዴሞክራ
ቶች የተባሉትና የሱዳን ወዳጆች የነበሩት) የምዕራቡ ፀረ ሱዳን ሴራ ዋና ማዕከልና መሳሪያ ሆኑ።
ከያዝነው ርዕስ ጋር ቢገናኝም ወደ ሌሎች ርዕሶች ይወስደናል እንጂ ሶስቱ በአሜሪካ ዕቅድ መሰረ
ት በርዋንዳም በዛይርም የተጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከሶስቱ ጎንም በነሱ ወታ
ደራዊና የሰው ሀየልም እርዳታ ለስልጣን የበቃው የርዋንዳው ካጋሜ ተጨምሯል። በሺርም በአዲስ
አበባ የግብፁን ሙባረክ ሊያስገድል ያደረገው የከሸፈ ሙከራ መለስና ሱዳንን ለተወሰነ ወቅት
አጣልቶ ለወያኔ ተቃዋሚዎች በር ከፍቶ ነበር። ለማንኛውም የሱዳንን መፈራረስ ወይም መጠቃት
ና መበጥበጥ ፈላጊዎች ምዕራባውያን (ፈረንሳይን ሳይጨምር)፡ እስራኤል፡ ዩጋንዳ፥ካጋሜ፡ ወያኔና

ሻዕቢያ ነበሩ ማለት ይቻላል። ኤርትራም ከበሺር ከተጋጨች በኋላ የሱዳን ተቃዋሚ ሀይሎች ደጀ
ን ሆና የጋራንግም ተወካዮች ሆኑ የሰሜኑ የፖለቲካ ድርጅቶች በዚያው ሰፈሩ። የዳርፉርና የቤጃ
አማፅያንም ከሻዕቢያ እርዳታ ያገኙ ጀመር/ ነበር። በአሜሪካ የዓለም ንግድ ማዕከልን ለማፈንዳት
በተደረገው ሙከራ ከተያዙት ውስጥ አምስቱ የሱዳን ፓስፖርት የያዙ ከመሆናቸው ሌላ በአሜሪካ
ኖቹ የተጠለፈው የሱዳን ዲፕሎማሲያዊ የመልዕክት ልውውጥ የበሺር አገዛዝ በሙከራው እጎ ደነበ
ረበት በማረጋገጡ አሜሪካ በሱዳን ላይ ይበልጥ ጥርሷን መንከሷ የሚታወስ ነው። በወቅቱ ፈረንሳይ
ከበሺር አገዛዝ ጋር የነበራት ጥሩ ግንኙነትና ከአሜሪካም ጋር በርዋንዳና ዛይር ጉዳይ የነበራት ልዩ
ነትም በቀውሱ ሂደት ላይ የማይናቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።

2.4 በሴፕቴምበር 2008 የእስራኤል የፀጥታ ሀላፊ አቪ ዲሽተር ሲናገር " ሱዳን ሁሌም በውስጣ
ዊ ችግር የምትታመስ መሆኗን ማረጋገጥ አለብን" ማለቱ ብዙ ጊዜ ይጠቀሳል። ግብፅ ኢትዮጵያን
ን በተመለከተ ደጋግማ ያለችው ነው። የግብፅ ፖለቲካ በአባይ ጥያቄ የተቃኘ መሆኑ ሲታወቅ እስ
ራኤልም የምትበጠበጥ ሱዳን የግብፅም የእስራኤል ጠላቶችም ረዳት ለመሆን አለመቻሏን ከመፈለ
ጓ ሌላ በአባይ ውሀ ላይም ሊደበቅ የማይችል ፍላጎት እንዳላት ቀደም ሲል ማለትም በእስራኤል ም
ስረታ ጊዜ ቴዎዶር ሄርዜል ለእንግሊዞች ካቀረበው ጥያቄ የሚታወቅ ነው። በ1974 ም ምስራቅ
ኢየሩሳሌምን ለፍልስጤሞች ለቀን በምትኩ 840 ሚሊዮን ክዩብ የአባይን ውሃ እንውሰድ የሚለ
ውን ዕቅድ የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሜናሂም ቤጊንና እንዲሁም ኢትዮጵያና ሱዳን በመቃወማ
ቸው ከሽፏል። የካምፕ ዴቪድ ስምምነትን የግብፁ ሳዳት ከፈረሙም በኋላ የአባይን ውሀ ለማግኘት
ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦ ጉዳዩ የሁሉን የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ስምምነት ይጠይቃል በሚል ሳዳት
ውድቅ አድርጎታል። ለማንኛውም ሁኔታዎች ቢለዋወጡም የእስራኤል ቋሚ ፍላጎት የሱዳንን መዳ
ከምና መገነጣጠል መሆኑን ባለስልጣኖቹም አልካዱም። በጀኔራል ኤፍሬም ስኔህ ለቀረበ ጥያቄ ሲ
መልስ የእስራኤል የፀጥታ ሀላፊ አቪ ዲሽተር " የደቡብ ሱዳን ሁኔታ ከኮሶቮ የሚለይ አይደለም።
የቀድሞውን አቅዋማችንን በመቀጠል ደቡብ ሱዳን መገንጠሏን እንደግፍ። ፍጥጫን የሚደግፍን ሀ
ገር መረጋጋት ልንፈልግ አንችልም። ሱዳን እንደ ክሮአሺያ፣ ሰርቢያና ማሲዶንያ ልትሆን ትችላ
ለች። ይህን የመገነጣጠል ፍንዳታ በመደገፍ ጊዜ ለመግዛት መጣር አለብን። ግባችንንም በ2011 ለ
መፈፀም ተስፋ እናደርጋለን " ሲል ተናግሯል።አሜሪካና እንግሊዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ አክራሪ
እስላምነትንና ሽብርን እንዋጋለን ባይ ናቸውና፣ የደቡብ ሱዳን አብዛኛው ሕዝብ ክርስቲያን ነው
በሚልና ሱዳን ሽብርተኛ ነውና መዳከም አለበት በሚልም የሱዳንን መገነጣጠል ድግፈው ቀጥለዋ
ል። ከዚህ ሌላም የደቡብ ሱዳንን ማዕድን፣ ዘይትና ሀብት ለመቀራመት የአሜሪካን ኩባንያዎች ከአ
ሁኑ ጀምሮ ( ሞቡቱ ከመውደቁ በፊት ከሚቹ ካቢላ ጋር እንዳደረጉት ሁሉ) ከደቡቡ አገዛዝ ጋር
እየተፈራረሙ ናቸው። በዚህም መሰረት የአሜሪካዊው ሀይልበርግ ኩባንያ በዩኒቲ ስቴት ከኑዌሩ ጀ
ኔራለ ፓውሊኖ ማቲፕ (ከሪያክ ማሻር ጋረ ከጋራንግ ተገንጥሎ የበሺር ታጣቂ ሆኖ የነበረው) ጋር
በመፈራረም 400 ሺ ሄክታር ለምና ባለማዕድን መሬት ተመርቻለሁ እያለ ነው (ይኸው ሀይልበርግ

ናይጄሪያና ኢትዮጵያም ይገነጣጠላሉ በሚል ኢትዮጵያን በተመለከተ በአማካሪነት የኦጋዴን ግንባ
ርን መሪዎችና ከጋምቤላ ደግሞ የደርግ ባለስልጣን የነበረውን ቱሀት ፖልን በአማካሪነት መቅጠሩ
ንም ገልጿል) ። ወያኔ ደቡቡንም ሰሜኑንም እያስተናገደ በአንድ በኩል በሺርን መሬት ሰጥቶ ሲያ
ግባባ በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ የምዕራቡ ጉዳይ አስፈፃሚ ለመሆን ከመነሳቱ ሌላ በጋምቤላ ላይ
እነ ሪያክ ማሻር የሚያነሱትንም የግዛታችን ነው ጥያቄ እስተናግዳለሁ እያለ ነው። ኤርትራ በበኩ
ሏ ሰልፏን ከሱዳን ጎን ካደረገችና መገንጠል አይበጅም ካለች የተወሰኑ ዓመታት አልፈዋል። ግብፅ፣

ሊቢያና ተያይዞም አረብ ሀገሮች የሱዳንን መገንጣጠል የማይፈልጉ ሲሆኑ ግብፅ በተለይ በደቡብ ተጀምሮ የነበረው የጆንግሌ ካናል ዕቅድና ደቡብ ሱዳን ሌላ ራሷን የቻለች የነጭ አባይ ተፋሰስ ሀገር ልትሆን መነሳቷ ( ከሱዳን በስተቀር ብዙዎቹ የግብፅን የአባይ  አቅዋም ተቃዋሚ ናቸውና ) ያሳስባታል:: ዩጋንዳም የራሷ የመስፋፋት ዕቅድ አሁንም ያላት ሲሆን የደቡብ ሱዳን መገንጠል ሱዳን ለፀረ ሙሴቬኒው የጆሴፍ ኮኒ ትሰጥ የነበረውን ድጋፍ ያስቆማል የሚል ተስፋም አላት::

<u>3/ ምን ይከተላል?</u> እንደተጠበቀውና ሲቀሰቅስም እንደቆየው የደቡብ ሱዳን ሕዝብ በአብዛኛው መገንጠልን መርጧል:: ቁልፍ የሆነችው የዘይት ግዛት አቢዬ ገና ድምፅ አልሰጠችም--የደቡብ አካል ትሁን የሰሜን ገና አልተወሰነም:: ሌላም የድንበር መካለል ችግር በደቡብ ኮርዶፋን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቦታዎች አለ:: ስለዚህ  ታስረው የነበሩ አጋንንት ሁር ወጡ እንጂ  ተገርተው አላረፉም:: የደበቡን መገንጠል የበሺር መኮንኖች ሁሉ ተቀብለው ፀጥ ይላሉ ወይስ አስገነጠልክ ብለው ይገለብጡታል የሚለውም ጥያቄ እየቀረበ ነው::

በደቡብ የጀመረው ወደ ሌሎች የሱዳን ግዛቶችና ሕዝቦችም ዘንድ ሊዛመት የሚችል ነው:: በአፍሪካ ደረጃም የግንጠላው ወረርሽኝ ሊሰራጭ ይችላል--በተለይ ታላላቅ የአፍሪካ ሀገሮችን ማሰባበር የሚል የምዕራባውያን ዕቅድ አለና:: ደበቦችም ራሳቸው እርስ በርስ ሲዋጉ ባለፉት ዓመታት ከ 25 ሺ ሰው ያላነሰ አልቋልና ከግንጠላው በኋላ ውስጣዊው የስልጣንና የጎሳ ልዩነት መባባሱና ለግጭት ማምራቱም የሚጠበቅ ነው:: በአቢዬ ለምሳሌ በሚሲሪያ ዘላን አረቦችና በዲንካዎቹ መሀል ግጭት ተጀምሯል:: ሺሉኮች ከዲንካዎች በመሬት ጥያቄ ሲዋጉም ቆይተዋል:: የደቡብ ሱዳን መከላከያ ጦር የተባለውም በስም ብቻ እንጂ በደቡብ ሱዳን ያሉት ጦሮች የጎሳ ሀይሎች/ታጣቂዎች ለመሆናቸውና በርካታ የጦር አበጋዞችም አሁንም ከነትጥቃቸውና ተከታዮቻቸው መኖራቸው ምስጢር አይደለም:: የደበቡ መሪ ሳልቫ ማያርዲት ኪር ከወዲሁ በሙስና የተወዘዘ ከመሆኑ ሌላ አዲሲቷን ሀገር ለመምራትም ችሎታ የለውም ተብሏል:: ስለዚህም የደቡብ ሱዳን መገንጠል ቢያንስ ለመጪው ዓመታት ለአካባቢው ሰላም የሚበጅ ላይሆን ይችላል:: የደበብ ሱዳንን እንቅስቃሴ ኢትዮጵያውያን የረዱ ቢሆንም እነ ሳልቫ ኪርም ሆኑ ሪዬክ ማሻር ከወያኔ መቀራረቡን መምረጣቸው የታየ ነው:: ይህ ግን የማይቀየር ነው ማለት ባይሆንም ለመቀየር የሚፈልገውን የዋሺንግተንና ለንደንን አቅዋም ለውጥ መሆኑ ግልፅ ነው:: የምዕራባውያንን አቅዋም ለማስቀየር ደግሞ ትግልን በሀገር ማፋፋም ያሻል:: ከአፍቅሮ አሜሪካው ጎራ ኤርትራ ብትወጣም ደቡብ ሱዳን መለስን፣ ካጋሜን፣ ሙሴቬኒን ወዘተ በመቀላቀል በአካባቢው ተጨማሪ የምዕራቡን ጉዳይ አስፈፃሚ መሆንዋ የሚቀር አይመስልም:: ይሄ ሁሉ በሕዝብ ላይ ምን እንደምታ ይኖረዋል? ለአጭር ጊዜና በረጅሙ?  ይህንና መሰል ጥያቄዎችን ከሀገርና ሕዝብ ጥቅም አንፃር በጥሞናና በተገቢው መንገድ መመርመር ይገባል እንጂ ወርቁም ሚዛኑም ጠፋባቸው በሚያሰኝ መንገድ የባጥ የቆጡን መቀባጠር፣ ወዳጅና ጠላትን አለመለየትና አሳፋሪ ጥራዝ ነጠቅነትን ማንፀባረቅ ያስገምታል፣ያደናግራል እንጂ ምንም ጠቀሜታ የለውም::